# ሕዝብ ነው ሕይወቱ

(ከነቅዓ ጥበብ)

የውስጥ ደካሞች፣ በከንቱ አትታክቱ፣
ቅንጅት አይሞትም! ሕዝብ ነው ሕይወቱ!
        ጥቂት ግለሰቦች፣ አሜሩ አላሜሩ፣
        ማንም አይነቅለውም፣ ልባችን ነው ሥሩ።
አያሌ ታጋዮች፣ በእሥር ቢገኙም፣
መንፈሱ አልታሰረም፣ በውስጥም በውጭም።
        የቅንጅት መንፈስ፣ በሕዝቡ ላይ ሰፍሮ፣
        በሕይወትነቱ፣ ይኖራል ተከብሮ።
የብዙኃን ጋሻ፣ ቅንጅት ነሐስ ነው፣
ጦርም ሆነ ጥይት፣ አይችልም ሊበሳው።
        አንጃዎች ታረሙ፣ ከተንኮል ዕረፉ፣
        ከትዝብት በስተቀር፣ ምንም አታተርፉ።
        ከሐቁ ተማሩ፣ ከምርጫው ከሠልፉ፣
        የቅንጅት መሪ፣ ሕዝቡ ነው አትልፉ።
ፈተና ቢበዛም፣ ውጥኑን ለማፍረስ፣
በቀላሉ አይደክምም፣ የቅንጅት መንፈስ።
        በሕዝብ የሠረጸን፣ የነፃነት መንፈስ፣
        ቡድንም ሆነ አንጃ፣ አይችልም ለማፍረስ።
ቅንጅት መንፈሱ፣ የሕዝቡ ዋስትና፣
ሊረበሽ አይችልም፣ በቀላል ፈተና።
        የቅንጅት ችግኝ፣ በሕዝብ የታጠረ፣
        ያብባል፣ ያፈራል፣ ደን እያስከበረ።
የቅንጅት አትክልት፣ ፍሉም ሆነ ዘሩ፣
በለምለም መሬት ነው፣ የበቀለው ሥሩ።
        ቅንጅት መንፈሱ፣ የብዙኃን ተሥፋ፣
        መች ተበገረና፣ ለአግአዚ ጭፍጨፋ።
በሕዝብ የታጠረው፣ የሰማዕታት ተክል፣
በታጋዮቹ ደም፣ ያብባል ያፈራል።
የኔን ልንገራችሁ፣ የናንተን አላውቅም፣
የቅንጅት መንፈስ፣ በፍጹም አይደክምም።
        እንደው ለምናልባት፣ ትንሽ የተረፈ፣
                        ህሊና ካላችሁ፣
        አንጀኞች ጮሌዎች፣ እፈሩ እባካችሁ፣
        የሰማዕታቱ ገድል፣ ልቡና ይስጣችሁ፣
        ኤሎሄ ጥሪያቸው፣ እስኪ ይሰማችሁ፣
        ደማቸው ይጮሃል፣ የትም አይለቃችሁ፣
        በህዝባዊ ችሎት፣ ፍርዱን ሳይሰጣችሁ!

Posted on www.debteraw.com by courtesy of the author

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com